# መግቢያ

የሚቀጥለው ግጥም ገበሪን፤ እርሻንና ጎዋሮን፤ እንደ ውስጠ ወይራ በመጠቀም ብሶትን ያንጎራጉራል። ደራሲ ለምለም ጸጋው።

በሰሜን ኢትዮጵያ እርሻ ማለት ሰፋ ያለ ማሳ (መሬት) ገበሮች ደጋግመው አርሰው ሲሆን ለንግድ ጭምር አለበለዚያ የዓመት ቀለብ ለቤተሰባቸው የሚያመርቱበት ቦታ ነው። ለምሳሌ ጤፍ፤ ሽንብራ፤ ዳጉሳ፤ ኑግ፤ ዘንጋዳ፤ ወዘተ የሚባሉ የእህል አየነቶች ናቸው።

ጎዋሮ ግን አነስተኛ የሆነ ቦታ ከቤታቸው ጥግ የሚገኝ በሬም ባይኖራቸው በመቆፈሪያ አለስልሰው ጎመን፤ ድንች፤ ወይም በቆሎ ለጊዚያዊ ምግብ የሚያመርቱበት ቦታ ነው።

## አረ ለማን ልንገር?

ኡ! ኡ!
አረ ለማን ልንገር?
ህግ የበላይ ሆኖ
መብት እንዲከበር፤
በኢትዮጵያ ምድር።

ኡ! ኡ! የሰው ያለህ
አረ ለማን ልንገር
ለማንስ ላስረዳ
የኢትዮጵያን እሮሮ
ጣራ ጋራው ፈርሶ
እርሻ ሆኖዋል ጉዋሮ

እንዲያው ባጠቃላይ
አረ ለማን ልንገር?
የኢትዮጵያን ችግር!

እርሻው ሁሉ ቀርቶ
ጎዋሮ በመሆኑ አይደለም ጭንቀቴ፤
ወጣት ሽማግሌው ስለታቆረ ነው
በዚያ በቃሊቴ።

ኡ! ኡ! ለማን ልንገር?
ሕግ የበላይ ሆኖ
ቅን ፍርድ እንዲሰፍን
በኢትዮጵያ ምድር።
ይገርማል ይደንቃል አረ ለማን ልንገር?
የለምን ሰማሁኝ
በዚያ በፓርላማ ሕግን የሚያረቅቅ፤
ጭቆናን አውግዞም
ቅን ፍርድን የሚያጸድቅ።
አንድም የለምና ከነጋዴ በቀር
አትልፊ አሉኝ ሰወች ለመሄድ ፓርላማ፤
መሪት ላራሽ ባዩን አዳምጦ የሚሰማ።

በሩቅ የሚጣራው እንዲህ ሲለኝ ሰማሁ
ገበሪ ነኝና ምስቅልቅል አላውቅም
የጥርቅም መንግሥት የሠጠኝን ጥቅም፤
የሚነግረኝ ሁሉ ምንም አልገባኝም
ገልጾም የሚያስረዳ ጠበቃ የለኝም።
አረም ትግሬ በቅሎ
እህል ስላጠፋ መሐል ድረስ ሸዋ፤
ፍርድ ቤት እንዳልሄድ
የለችም ብርቱካን ቅን ፍርድ ፈራጅዋ።

ኡ! ኡ! የሰው ያለህ
አረ ለማን ልንገር?
የኢትዮጵያን ችግር።
ገበሪው ወንድሜ ይሳቅ ወይስ ያልቅስ፤
አረም ትግሬ በቅሎ
እህሉን ሲያጠፋው መሐል ሸዋ ድረስ።

ይህን ግን አውቃለሁ
የኢትዮጵያ መሪት ቢታረስ ለስልሶም
እህሉን ያጠፋው አረም ብቻ አይደለም
ንጉሱ መለሰ በአዋጅ አስከትቶ
እህል እሳር ሳይለይ ስላሳረመው ጡዋት፤
የገበሬው ማሳ አልበቃም ለዓመት ምርት።

ያች ዳኛ ብርቱካን
የት ሄደች ዛሬ ጠዋት፤
ከስራ እንዳትውል ንጉስ ካስቀመጣት።

ብርቱካን ሚደቅሳ ቅን ፍራጅ መሆኑዋን
መለሰ ገብቶታል ማለትን ስሰማ
ግርም አለኝ እኔ፤
እውነትም መሆኑን በስራ ገለጸ
ሚደቅሳን ሲለውጥ በታምራት ላይኔ
አወይ ግሩም ስርዓት
የምስቅልቅል መንግስት፤
የቆመው ለሴት መብት
አንድ አይበቃም ብሎ
አስር ወንድ ዘረፋት።

አገሬ ኢትዮጵያ ምን ንጉስ አስቀመጥሽ
ከዚያ አዲስ ዙፋን
ደምስሶ ባሕልን
በአዋጅ አስነግሮዋል
በኮበሌ ጅራፍ፤
ሁሉም እንዲገረፍ።
ምስክር ልጥራ ወይ እውነት ካስፈለገ
ከሐረር መቀሌ፤
ሐሰት የማያውቀው
አለልኝ መስፍኔ።
ኡ! ኡ! በሕግ አምላክ
አረ ለማን ልንገር?
ሕግ የበላይ ሆኖ
መብት ለማስጠበቅ
በኢትዮጵያ ምድር።
ትግሬ ነሽ ይሉኛል
ተከዜን ስሸገር
እስላምም ነሽ አሉኝ
በምስጊድ ባለፍሁኝ
ኦረሞ ነሽ አሉኝ
ነቀምት ስላደርሁኝ
ሲዳማ ነሽ አሉኝ
ጥቁር ወንዝን በጠዋት ስለተሻገርሁኝ

ሱማሌም ነሽ አሉኝ
ሐረር ድሬዳዋ ምሳየን በልቸ
ጫት ሳይቀር ባኘክሁኝ

ኡ! ኡ! በሕግ አምላክ
አረ ለማን ልንገር
እጅግ ተጨነቅሁኝ፤
ምነው መጠለያ መጠጊያ ያጣል ሰው
እኔ ኢትዮጵያዊ ነኝ
ብየ ባስታወቅሁኝ።
እምብኝ አሻፈረኝ አትላኩኝ ፓርላማ
ብሶቴን ለማፍሰስ፤
ከማጎብደድ በቀር ለዘናዊ ንጉስ
መች በግሩ ቆመና።
ተው አታስገድዱኝ አቤቱታ እንዳቀርብ
ለዚያ ለፓርላማ
የፓለቲካው ጎርፍ ጠርጎ እንዳያጠፋኝ፤
ለራሱም ዋና አያውቅ እንኩዋን ሊያሻግረኝ።
ይልቅ በሲትነት አዜብን ልጠይቃት፤
ተሻግራለችና በዚያ በወልቃይት።
የምስቅልቅል መንግስት
ስርዓቱ እንዴት ነው ምን ወንዝስ አፈራው
ማንስ ቢያንጸው ነው፤
ኢትዮጵያን በመላ በፍርሃት የሚያየው
ሕዝብን ሲያስተዳድርስ ነውር የማያውቀው።

ኡ! ኡ! በሕግ አምላክ
አረ ለማን ልንገር፤
የኢትዮጵያን ችግር!

አዜብ ትቅርና ትመስክር ብርቱካን
የምስቅልቅል መንግስት
መቆሙን ለሴት መብት፤
አንድ አይብቃሽ ብሎ
በአሥር ወንድ አዘረፋት።
እኔ ግን እላለሁ ከከርቸሌ አድኖዋት።
ደራሲ ለምለም ጸጋው፤
ታህሳስ 28, 2001/January 6, 2009